64
TW
AGR
017
c

# CHRISTIAN RELIEF & DEVELOPMENT ASSOCIATION

## Training Programme

## On

## Village Level Operation and Maintenance of Pump

CCRDA

*December 5 - 10, 1994*
*EMI*

የ ል ብ ረ ተ ሰ ብ  ተ ሳ ት ፍ

በ ገ ጠ ር  የ መ ጠ ጥ  ው ሃ  ፕ ር ጀ ክ ት

Community Management/Participation

in Village Water Supply Project

CCRDA

በገጠር ደረጃ በፓምፕ ስፕረሽን የገና ሥለጠና ላይ የቀረበ

Presentation on the Training of Trainers

for Village Level Operation and Maintenance

of Hand Pumps

## 1. መ ገ ቢ ያ ፣

የኅብረተሰብ ተሳትፎ በተለያዩ አመለካከቶች ሰፊ ትርጉም ይሰጠዋል:: ሆኖም ፅንሰ-ኃሣቡ የሚያንፀባርቀው ሰዎች ኑሮአቸውን የተመለከተ የለማት ፕሮገራሞች ከዕቅድ አወጣጥ ጀምሮ ግንባታው ፍፃሜ አስከሚያገኝ ድረስና ከዚያም በኋላ አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በአስተዳደርና ጥገና ተፈላጊውን ክትትል፣ ቁጥጥር፣ ግምገማ በማድረግ ተጠቃሚው ማሕበረ-ሰብ የበኩላቸውን ሚና ሚጫወት አንዲችሉ ዕድል የሚያስገኝ ሂደት ነው::

ከተለያዩ የዕድገትና የለማት ዘርፎች ለምድ በመነሳት በገጠር የመጠጥ ውሀ ሥራ የተጠቃሚዎች ተሳትፎ ለግንባታና ለአስተዳደር ሥራው ቅልጥፍናና ለተሳካ ውጤት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አንዳለው ጠበብቶች አረጋግጠዋል:: በመሆኑም ከውጭ የብድርና የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን ድጋፍ ለማገኘት ለሚደረገው የብሔራዊ ፕሮገራሞች ገምገማ የኅብረተሰብ ተሳትፎ አንዱና ጠቃሚ መስፈርት አየሆነ መጥቷል:: በታዳጊ አገሮች በተለይም በአገራችን ከፍተኛ የገጠር ሕዝብ በብዛት በሚገኙበት የገጠር መጠጥ ውሃ ግንባታ፣ አስተዳደርና ጥገና ሥራዎች የሚጠይቅ ወጪ አጅግ ብዙ በመሆኑ መንግሥትና የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ከሚያደርጉት ጥረት ጐን የተጠቃሚው ኅብረተሰብ ተሳትፎ በተጠናከረ ሁኔታ "ራስን በራስ መርዳት" በሚለ መርህ መሠረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት በብርታት መቀጠል ይናርበታል::

## 2. ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች (Socio-economic Issues)

በአጠቃላይ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሠረት ለማት ነው:: ለማት አጠቃላይ ኢኮኖሚውንና ማሕበራዊ ሥርዓትን አንደገና ማዋቀርና አዲስ መለክ መስጠትን የሚያካትት ባለብዙ ፈርጅ ሂደት ነው::

ቀደም ባሉት ዓመታት የአንድ አገር አጠቃላይ ኢኮኖሚና ማሕበራዊ ዕድገት ለመገምገም በሕዝቡ ማሕበራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ላይ ሳይሆን ትኩረት የሚሰጠውና አንደ ዕድገት መለኪያነት የሚወሰደው በቁሳዊና ገንዘብ ነክ ሁኔታ ላይ ነበር:: በተለይ ከጠቅላላ የሀገር ሀብት (Gross Domestic Product) ወጥ የነፍስ ወከፍ ድርሻ (Per Capita real income) አንደ አድገት አመለካችነት ሲታይ ቆይቷል:: ይሁንና የአንዳንድ አገሮች (ለምሳሌ፣ ነዳጅ አምራች የሆኑት) የነፍስ ወከፍ ድርሻ ከፍ ብሎ ቢዘገብም፣ የብዙሀኑ የኑሮ ደረጃና ሁኔታ ግን ብዙ ለውጥ ሳይታይበት በመቅረቱ ከ1960ዎቹ ዓመታት ወዲህ ብቅና የዕድገት አመለካችነታቸው አጠያያቂ ሆኗል:: ስለዚህ የአንድን አገር አጠቃላይ ዕድ

.../

CCRDA

ገትና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለመገምገም ከዚህ አመለካች በተጨማሪ የጤና አገልግሎት ሥርጭት፣ የሕፃናት ሞት፣ ትምህርት፣ የንፁህ የመጠጥ ውሃ መስፋፋት፣ መጠለያ ... ወዘተ የመሳሰሉ አመለካከቶችን መገምገም አስፈላጊ መሆኑ በብዙ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ጠበብት ዘንድ አየታመ ነበት መጥቷል::

በዚህ ክስተትና በተለይም በገጠርና በከተሞች መካከል አየሰፋ ከመጣው የኑሮ ሁኔታ መራራቅ አንፃር ለገጠር ሕዝብ የኑሮ መሻሻል የሚያስፈልጉ ፕሮግራሞችን መንደፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ:: ስለዚህም ከ1970ያቹ ዓመታት ወዲህ ነብረተሰቡን በማሳተፍ የለማት ዕቅድ ከላይ ወደታች (Top-down) ብቻ ሳይሆን ከታች ወደላይ (Bottom-up) አንዲሆን በማድረግ አንደጤና፣ ትምህርት፣ ንፁህ ውሃ፣ መጠለያ ... ወዘተ የመሳሰሉት መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ የገጠር ለማት ስለት ተቀይስ በብዙ በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች አየተደረገ ይገኛል:: የገጠር ለማት ስለትም በከተሞችና በገጠር መካከል ያለውን የኑሮ ሁኔ ለዩነት የሚያጠብ፣ ነብረተሰቡን በማሳተፍና ቅንጅታዊ አሠራርን በማዳበር መሠረታዊ አገልግ ሎቶችን ለማዳረስ በመንግሥት ላይ የሚደርሰውን ጪና የሚያቃለል የለማት ስለት ነው:: በዚህ ሁኔታ የገጠሩን ነብረተሰብ አንገብጋቢና አሳሳቢ የሆኑትን በተለይ የመጠጥ ውሃ ችግሮችን በቅደም ተከተል ለመፍታት በሚያስችሉ ተግባሮች ላይ የሚያተኩር፣ የራስን በራስ መርዳት በሚለው መርህ መሠረት በነብረተሰቡ ንቁና ቀጥተኛ ተሳትፎ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባለሆኑ ዕርዳታ ሰጪዎች ትብብርና ቅንጅታዊ አሠራርን ያካተተ መሠረታዊ የገጠር ለማት ፕሮግራም መንደፍ አጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው::

## 3. <u>የነብረተሰብ ተሳትፎ ፅንሰ-ኃሳብ</u>

የነብረተሰብ ተሳትፎ ምንነቱንና ጠቃሚውን ዘርዝር ከማየት አስቀድሞ ቁልፍ የሆኑ ቃላት ላይ ማተኮረ በቀላሉ ግንዛቤ ያስጨብጣል:: በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የነብረተሰብ ተሳትፎ ቁልፍ ቃላቶች በጥቂና አንመለከት:-

### ሀ. <u>ነብረተሰብ/ማሕበረሰብ</u>

በአንድ የተወሰነ የመለክአ ምድር አካባቢ ወይም ቅርበት በቋንቋ፣ በባሕል፣ በለዩ ለዩ ጥቅምና ፍላጉት ላይ የተመሠረተ የተቀራረበ ግንኙነት በመፍጠር በማሕበ ራዊ ሥርዓት ተሳትፎ የሚናር ሕዝብ ነው::

CCRDA

ለ. ተ ሳ ት ፍ

ሰዎች ሕይወታቸውንና ኑሮአቸውን ለማሻሻል በሚታቀዱ ወይም በሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ረገድ በየደረጃው ከዕቅድ አወጣጥ ጀምሮ እስከ ኘሮጀክቱ ፍፃሜ ድረስ የመካፈል አድል ሲያገኙ ነው:: በዚህ መሠረት የልማቱ ተጠቃሚ ነብረተሰብ:—

1. ፍላጐቱንና ምርጫውን ለመግለጽ ዕድል በመሰጠት በውሣኔ ላይ እንዲያናር ማድረግ፤

2. አስፈላጊ መረጃዎችን አንዲያውቃቸውና አስተያየት አንዲሰጥባቸው ዕድል መሰጠት፤

3. ዕውቀቱን፤ ለምዱን፤ ጉልበቱንና ንብረቱን በማስተባበር በልማቱ እንቅስቃሴዎች ላይ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሲችል ተሳትፎ ... እንላለን::

ሐ. ለማት/ዕድገት

የአንድ ነብረተሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚለወጥበት የዕድገት ሂደት ነው:: ይኸውም:—

_ በአጠቃላይ የሰዎች መሠረታዊ ፍላጐቶች ተሟለተውና ተሻሽለው የኑሮ ደረጃቸው ሲያድግ፤

_ የተፈጥሮ ሀብትን ነብረተሰቡ በጋራና በአኩለነት የተጠቀመባቸው የሆነ እንደሆነ፤

_ በነብረተሰቡ ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ በመፍጠር ሁሉም ለለውጥና ለዕድገት ያለው ጥሪ አመለካከትና ተቀባይነት ሲኖር፤

_ በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚ፤ በሶሻለና በባሕል ኑሮ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች አኩለ የሚታዩበትና በአኩለነት የሚሳተፉበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው::

በርካታ ተመራማሪ ምሁራን ስለነብረተሰብ/ማሕበረሰብ ተሳትፍ ዕድገት/ለማት በርካታ ድርሰቶችን ጽፈዋል:: ብዙም ብለዋል:: ከአብዛኛቹ አስከበሪዎና ዊን ፊለድ የተባሉት ምሁራን ስለ ብሔራዊ ዕድገት ወይም ሥለጢኔ አንዲህ ሲሉ አጠቃለውታል "በአንድ አገር ውስጥ በሶሻለና በኢኮኖሚ የሚከሄዱ ለውጦች ናቸው፤ የአነዚህ ለውጦች ሂደት ደግሞ ከጥንታዊ ወደ ዘመናዊ የሕይወት ሥርዓት ነው::"

.../

CCRDA

## 4. የኅብረተሰብ ተሳትፍ በልማት በተለይ በመጠጥ ውሀ ሥራ ለምን አስፈለገ ?

የልማት ዕቅድ አውጪዎች በተጠቃሚው ኅብረተሰብ አውነተኛ ፍላጐትና ችግር ላይ ያለ ተመሠረተ ከአካባቢው ዕውቀትና ባሕል ጋር ያለተጣጣመ የልማት ፕሮግራሞችን በመንደፍ ከላይ ወደታች ተወሰነው ሲያካሄዱ ቆይተዋል:: በመሆኑም የተጠቃሚው ኅብረተሰብ ዕውቀት፤ ለምድ፤ ሀብትና ፍላጐት ሳይታከለበት የልማት ዕቅድ አውጪዎች በኢኮኖሚ ሁኔታና በቴክኒክ ሥራው ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ የተሰሩ ከፍተኛ ወጪ የፈሰሰባቸው የመጠጥ ውሀ ተቋሞች ከተከናዉኗው ውስብስብነት የተነሳ ለአጠቃቀም አስቸጋሪ በመሆናቸውና ለአካባቢው ባሕልና ዕውቀት ባዕድ በመሆናቸው በተገለጋዩ ዘንድ በቂ እንክብካቤና ተቀባይነት ሳያገኙ እንደቀሩ ታውቋል:: በአሁኑ ወቅት አንኳን በአገራችን ውስጥ ከተሠሩት በርካታ የውሀ ተቋሞች አገልግሎት የማ ይሰጡ ከ60% በላይ ይገመታሉ:: ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለራሱ ጥቅም በሚሠሩት የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ላይ ከፕሮጀክቱ ዕቅድ ፅንሰኃሣብ ጀምሮ በየደረጃው ሁለገብ ተሳትፍ ባለመደረጉ ነው:: በመሆኑም በፕሮጀክት ዕቅድ አወጣጥ ላይ ኅብ ረተሰቡ የበኩሉን ኃላፊነትና አስተያየት ሰይጠየቅ ከሌላ አቅጣጫ የወጣውን ዕቅድ አንዲያሰፈጽም ብቻ ከተደረገ በፕሮጀክቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት ስለማይኖርበት ኃላም ለአገልግሎቱ ተቋም አስፈላጊውን አንክብካቤና ጥበቃ ላያደርግ ይችላል:: በመሆኑም በማንኛውም የልማት ፕሮጀክት በተለይም አንደ የአጅ ፓምፕ ባሉ በመጠጥ ውሀ ሥራዎች በየደረጃው ግለት በዕቅድ አወጣጥ፤ በግንባታ ሥራዎች፤ በአንረሽንና ጥገና አንደዚሁም የአገልግሎቱን ሁኔታዎች በመከታተል፤ በመቆጣጠርና በመገምገሙ ሁሉ ተገለጋዩ ኅብረተሰብ ንቁና አውነተኛ ተሳትፍ ማድረግ አጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል:: የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶቸም የሕዝቡን ተሳትፍ በዕቅድ ውስጥ መታከል አንዳለበት አበክረው የሚጠይቁት ለልማት ስትራተጂ የተጠቃሚውን ሕዝብ በሁሉም ደረጃ ማሳተፍ የባለቤትነት ስሜት ለመፍጠር ተሳትፍ መሠረታዊ በመሆኑ ነው:: በመልማት ላይ ያሉ በርካታ አገሮች የኅብረተሰብ ተሳትፍ ጽንሰኃሣብ ዐለማቸን ተግባራዊ በማድረግ የተጠቀሚው ሕዝብ የሥራ ጉልበት፤ የገንዘብና የአካባቢ የገንባታ ቁሳቁስን በማስ ተባበር ከፍተኛ ገምት የሚሰጧቸው የልማት ሥራዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ:: በአገራችን ይህንን የኅብረተሰብ ተሳትፍ ስትራተጂካዊ አሠራር በመጠቀም ሰፊው የገጠር ሕዝብ ከተለያዩ የጣሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ንቁ ተሳትፍ አንዲያደርጉ ብርቱ ጥረት ማድረግ ይገባል::

.../

CCRDA

## 5. በገጠር ለግት ሥራዎች በተለይ በመጠጥ ውሃ ኘሮጀክት ንቁና አውነተኛ የነብረተሰብ ተሳትፍ የሚያስገኙ ጥቅሞች

5.1 የመጠጥ ውሀ አገለግሎት በአጥር ጊዜ ውስጥ አንዲዳረስና አንዲስፋፋ ይረዳል::

ራስን በራስ መርዳት በሚለው መርሆ መሠረት ነብረተሰቡ የአካባቢውን ዕውቀት፣ ለምድ፣ ጉልበት፣ ግቴሪያልና ገንዘብ በማስተባበር የንፁህ መጠጥ ውሃ በገጠሩ አንዲስፋፋ ያደርጋል::

5.2 የውሃ ተቋማት በአነስተኛ ወጪ አንዲሠሩ ያስችላል::

በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖረውን ሕዝብ ችግርች መሠረት በማድረግ ሚዘናዊ የሆነ መፍትሔ አንዲያገኝ ያስችለል::

5.3 በራስ መተማመን ያሰገኛል::

አንድ የመጠጥ ውሃ ኘሮጀክት የሕዝቡ ተሳትፍ አጥጋቢ ውጤት ሲያስገኝና የተሰካ ሲሆን ተሳትፍው በራሱ የመተማመን ስሜት ስለሚያሳድር የአካባቢውን ለማት ያፋጥናል::

5.4 ለዕድገት የሚያቅጥ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል::

ነብረተሰቡ በራሱ ጥረት አጥጋቢ ውጤት ከያ በኋላ ሌሎችንም ችግርች ለመፍታት አን ደሚችል ስለሚረዳ ማናቸውንም ችግርች በጋራ ጥረት ለመፍታት ይነሳሳል፣ ይነቃቃል:: ባገኘው ለምድ ምን ማድረግ አንዳለበት፣ ማንን ማነጋገርና አንዳት ለሠራ አንደሚችል ስለሚረዳ ጥረቱን ይቀጥላል::

5.5 የባለቤትነት ስሜት ያሳድራል::

ሕዝቡ በራሱ ወጫኔና ተሳትፍ የሠራውን ሥራ አንደራሱ ሥራ አድርጉ ስለሚመለከተው በኘሮጀክቱ ይኩራል፣ በአገልቡ ይጠቀምበታል::

5.6 የነብረተሰቡ አንገብጋቢ ችግርችን የሚፈቱ ኘሮገራሞች አንዲቀየስና አንዲሠራ ያደርጋል::

የኘሮጀክት ኃላፊነት ከማፍለቅ ጀምሮ ነብረተሰቡ ተገቢውን ተሳትፍ አንዲያደርግ ከተፈለገ በሚታቀደው ኘሮጀክት ሕዝቡ ያለበትን ከፍተኛ ችግር የሚያቃለል ይሆናል::

.../

CGRDA

5.7 ሥራዎች በትክክለ መሠራታቸውን ያረጋግጧል::

በፕሮጀክቱ የሥራ ደረጃዎች ሁሉ ሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ከደረገ ምንም አንኳን ቴክኒካዊ ሥራዎች ላይ የባለሙያዎች ውሣኔ የሚያስፈለግ ቢሆንም የቴክኒኩ ሥራ ከአካባቢ ሁኔታ ጋር አንዲጣጣም ያደርጋል:: የውጭውና የአካባቢው የቴክኖሎጂ ውህደትና ቅንጅት ይናራል::

5.8 በአካባቢ ያሉ ጠቃሚ ለምዴች አንዲዳብረ ያደርጋል::

ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ንቁ፤ ቀጥተኛና አውነተኛ የሕዝቡ ተሳትፎ ከታከለበት በአካባቢ ያሉ ጠቃሚ ባሕሎችና የሥራ ለምዴች ጋር ቅንጅት ይፈጠራል::

5.9 ሕዝቡን ከባለሙያዎች ጥገኝነት ያላቅቃል::

ንቁ፤ ቀጥተኛና አውነተኛ የነብረተሰብ ተሳትፎ ከባለሙያዎች የሥራ ለምድና የአሠራር ዘዴዎችን ትምህርት ሰለሚያስገኝ ቀስ በቀስ ነብረተሰቡ ከባለሙያ የተጣረው በተገበር በማለማመድ ራሱን አንዲችል ያስደርጋል::

5.10 ንቃተ-ሕሊናን ያዳብራል::

በሕብረተሰብ ተሳትፎ አማካይነት ተሳታፊው ሕዝብ በራሱ ጥረት የራሱን ችገር ለመፍታት በሚያደርገው አንቅስቃሴ ውስጥ ትምህርቶችን ይቀስማል፤ የወደፊት ዕድገቱን ማሰብ ይጀምራል፤ በጋራ የመሥራት አስፈላጊነትን ይገነዘባል፤ የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውንም በመለየት ንቃቱን ያዳብራል::

## 6. የነብረተሰብ ተሳትፎ ሥራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ለደረጉ የሚገባ (Implementation Procedures)

የለማት ፕሮግራም በተለይ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት በአንድ ድርጅት ብቻ የሚሠራ ሳይሆን ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን የለማት ዘርፍች ትብብርና ድጋፍ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ፤ የመጠጥ ውሃ ሥራን በቡድን መሥራት ያስፈልጋል:: ይኸውም ከገብርና፤ ከትምህርት ሚኒስቴር፤ ከጤና ጥበቃ ሚ/ር ሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የገጠር ለማት አራማጅ ድርጅቶች የሥራ ፕሮግራም ጋር ተቀናጅቶ መሠራት ይናርበታል:: ይህም

.../

CCRDA

አንድ ዓይነት ሥራ አንዳይደጋገም፤ ጊዜና ጣቴሪያል አንዳይባክን ከመርዳቱም በላይ የተለያዩ ዕውቀቶችንና ለምደኞችን ያለዋውጣል::

በጣንኛውም የለጣት ሥራ ላይ የነብረተሰቡ ተሳትፍ፤ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቅንጅታዊ አሠራር ከፍተኛ ጠቀሚታ አለው:: ከሁሉ በላይ ግን ተጠቃሚ ነብረተሰብ ለኘሮጀክቱ ሥራዎች ስኬታማነት ወሳኝና ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: በመሆኑም የሕብረተሰቡ ተሳትፍ የሥራ አንቅስቃሴዎች በትክክለ ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህ በታች የተመለከቱ ድርጊቶች በቅደም ተከተለ (Implementation Procedures) መከናወን ያስፈልጋል::
አነዚህ ድርጊቶች:—

1. የለጣቱን ቦታውን/አካባቢውን ለጣጥናት በቅድሚያ ወደነብረተሰቡ መሃድና አብር በመ ቆየት ባሕሉን በጣጥናት፤ ኑርውን በመናር መገባበትና የነብረተሰቡን ተቀባይነት ግገኘት ያስፈልጋል:: በዚህ ሂደት ውስጥ በአካባቢው ተሳጭነት ያሊቸው ገለሰቦችን በቅድሚያ መቅረብ ያስፈልጋል::

2. ጣንኛውም የለጣት ሥራ በተለይ የገጠር መጠጥ ውሃ ኘሮጀክት ከመጀመሩ በፊት ተጠቃ ጩው ነብረተሰብ አስቀድሞ ጥቅሙን አንዲያውቅ ስለለጣቱ ኘሮገራም የተለያየ የጣስተ ጣሪያ ዘዴዎች በመጠቀም በቂ ትምህርት ወይም ስለኘሮጀክቱ በትክክለ አንዲረዳ ጣድ ረግ፤

3. የለጣቱ ኘሮገራም የተፈለገውን ገብ አንዳመታ የጚመለከታቸውን የገጠር ለጣት ዘርፍች ትብብርና ድጋፍ በቅድሚያ መፈለግ::

4. ስለአካባቢው ሁኔታና ለለጣቱ ኘሮገራም አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት፤ የገንዘብ ምንጭ፤ የአካባቢው ዕውቀትና ለምድ በአጠቃላይ ስለክለሉ የጣሕበራዊና ኢኮኖጚያዊ ሁኔታዎች በቂ መረጃ መሰብሰብ::

5. የነብረተሰቡ ተሳትፍ ሥራዎችንና የለጣት ኘሮገራሙን የጚያስፈጽም ከኘሮጀክቱ ተጠ ቃጚዎች በዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ከ5—7 አባላት ያሉትን አንድ ኮጚቴ መርጠ መሰየም፤ ግቷቋም::

.../

CCRDA

6. ኅብረተሰቡ በግንባታ ፕሮግራም የሚሳተፍበትን ዘዴ መቀየስ፤ ተሳትፍውን በማን? በምን? እንዴት? ምን ያህል? ከማን ጋር? መቼ? እንደሚደረግ መግለጽ፤ በግንባታ የሚደረግ የሕዝብ ተሳትፍ የምርት ጊዜን በማያዛባ መንገድ ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ መቀየስ ትኩረት የሚገባው የነርው የሕዝብ ተሳትፍ ሥልት ነው::

## 7. በገጠር ለማት በተለይ በመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት የኅብረተሰብ ተሳትፍ ዓይነትና መጠን

ኅብረተሰብን በማናቸው የለማት ፕሮግራም ማሳተፍ ለፕሮጀክቱ ዓለማና ገብ መሰካት የስትና ይሆናል:: በመሆኑም በለማት ሥራ በተለይ በገጠር መጠጥ ውሃ ከጅምረ በቅድመ ጥናት፤ በግንባታ፤ በአገረሽን፤ በጥገና፤ በአስተዳደር በክትትል፤ በቁጥጥርና በግምገማ ማሳ ተፍ ያለው ጠቀሜታ በዝርዝር ከላይ ተገለጿል:: በመሆኑም ሕዝቡ አምናበት ፕሮጀክቱ ወይም ተቋሙ የራሱ ንብረት መሆኑን ተገንዝቦ ለዘለቄታው የውሃ ጢቢያውን በአንክብካቤ እንዲይዝ በየደረጃው የሚያደርገው ተሳትፍ ወሣኝነት አለው:: የኅብረተሰብ ተሳትፍ ዋና ዓለማም ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ነው:: በመሆኑም ኅብረተሰቡ በገጠር መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ዋና ዋና ደረ ጃዎች ሊያደርገው የሚችለ የተሳትፍ ዓይነትንና መጠንን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከት፤

### 7.1 በፕሮጀክት ቅድመ ጥናት ደረጃ ከተጠቃሚው ኅብረተሰብ የሚጠበቅ ተሳትፍ፤

ቅድመ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ማንርውም ዓይነት መረጃዎች መሰብሰቢያና ማጠናከሪያ ደረጃ በመሆኑ የአካባቢው ሕዝብ ደግሞ ስለክለሉ የበለጠ ዕውቀትና ግንዛቤ ስለሚና ረውና ትክክለና መረጃዎችን ለመስጠት ስለሚችለ ለመረጃ አሰባሰብ አስፈላጊውን አገዛ ስለሚያደርግ ፕሮጀክቱ ገቡን እንዲመታ ከፍተና ሚና ይጫወታሉ:: በመሆኑም በቅድመ ጥናት ደረጃ ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ተሳትፍ ዓይነትና መጠን:—

- ስለአካባቢው ማሕበራዊና ኢኮናሚያዊ መረጃ መስጠት፤
- የታቀደው ፕሮጀክት ትክክለና የሕዝብ ፍላጉትና ችገር መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ከአጥኚው ባለሙያ ጋር መተባበር፤ ሃሣብና መረጃ በመስጠት ማገዝ፤
- ፕሮጀክቱ የሚሠራበትን ቦታ በመጠቆም፤ በመረጥና በመወሰን መሳተፍ፤
- ለፕሮጀክቱ የተከለለውን መሬት በመከለል፤
- ተስማሚ የቴክናሎጂውን ዓይነት በተቻለ አቅም፤ ዕውቀት መምረጥ፤

.../

CCRDA

_ የውሃ ግደያ ቦታዎች በመምረጥ፤

_ ሊያደርጉ የሚችሉትን የተሰትፍ ዓይነትና መጠንን በመግለጽ፤

_ ሥራውን ለሠራ የሚችለበትን ጊዜ በመወሰንና ዕቅድ በማውጣት፤

7.2 <u>በፕርጀክቱ ግንባታ ደረጃ ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ተሰትፍ፤</u>

ግንባታ የታቀደው የገጠር መጠጥ ውሃ ፕርጀክት ተግባራዊ የሚሆንበት ደረጃ ነው:: በመሆኑም የፕርጀክቱ ግንባታ በታቀደው ሁኔታ ለማከናወን የአሠሪው ድርጅትና የኅብረተሰቡ ተሰትፍ ሥራዎች፤ የተቀናጀ የማቴሪያል፤ የገንዘብ፤ የሰው ኃይል ወዘተ ... ትብብርና ድጋፍ ወሳኝ ነው:: በመሆኑም በዚህ ደረጃ የሚደረጉ የተሰትፍ ዓይነትና መጠን የሚከተሉት ናቸው::

1. የጉለበት ሥራ

_ ለዩ ሙያ የማይጠይቁ የጉለበት ሥራዎች መሥራት፤

_ የመንገድ ጠረጋ፤

_ የውሃ ቧንቧ መስመር ቁፋር፤

_ የንብረት ጥበቃ፤

_ የሳይት ወይም የፕርጀክቱ ቦታ ምንጠር ወዘተ ...

2. ከባለሙያዎች ጋር በመሆን የግንባታውን ሥራ ማስተባበር፤

3. ለግንባታው አስፈላጊና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁስ ... ድንጋይ፤ አሸዋ፤ አንጨት፤ ጠጠር፤ ኮረት፤ ወዘተ... ማቅረብ፤

4. ለግንባታ ሠራተኖች አመቺ ሆኖ ሲገኝ መጠለያና የዕቃ መጋዘን ማዘጋጀት፤

5. የግንባታውን ወጪ ለማገዝ አቅም በፈቀደ ሁኔታ የገንዘብ አስተዋጽኦ ማድረግ፤

7.3 <u>በገጠር የመጠጥ ውሃ አስተዳደር፤ አነረሽንና የገና ወቅት ከተጠቃሚ ኅብረተሰብ የሚጠበቅ የተሰትፍ ዓይነትና መጠን፤</u>

በአብዛኛው የኅብረተሰብ ተሰትፍ ከግንባታ ሥራ በኋላ ስለሚቃረጥ ብዙ ወጪ ተደርጉ ባቸው የተሠሩ አያሌ የገጠር መጠጥ ውሃ ጣቢያዎች <u>በለቤት አንደሌለው ንብረት</u> ከአጠ ቃቀምና ከጥንቃቄ ጉድለት የተጠበቀውን ግለጋሎት ሰይሰጡ ከጥቅም ውጭ ሲሆኑ ይታያሉ::

.../

CCRDA

ይህንን ችግር ለመቋቋም አንዱና ብቸኛ አሠራር ተጠቃሚው ኅብረተሰብ በውሃ ጥቢያዎች አስተዳደር፣ አነረሽንና የገና ንቁ፣ ቀጥተኛና አውነተኛ ተሳትፎ በባለቤትነት ደረጃ አንደራሱ ንብረት አንዲንከባከብ ማስቻል ነው:: ይህንንም በትክክለ ተጠቃሚ ሕዝብ ተረድቶ በጋራ ተወያይቶበት በዲሞክራሲያዊ ሂደት ከ5—7 አባላት ያለበት የውሃ ኮሚቴ ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት አቋቁመው አስፈላጊውን ተሳትፎ ማድረግ ዓይነተኛ የአሠራር ስልት ነው:: በዚህ መሠረት የተመረጠ ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባሮች በማ ከናወን የአስተዳደር፣ የአነረሽንና የጥገና ሥራዎች ያራምዳል::

1. ኅብረተሰቡን በመወከል ስለክለሉ የውሃ ችግር ጉዳዮችን ከሚመለከተው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣

2. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የውሃና የጤና ትምህርት አንዲሰጥ ያደርጋል፣

3. የውሃ ኘሮጀክቶች በየደረጃው በሚታቀድበት፣ በሚገነባበት፣ አገልግሎት በሚሰጥበት፣ በሚጠገንበትና ጠቀሚታው በሚገመገምበት ወቅት የኅብረተሰብ ተሳትፎ አንዲኖርበት ያደርጋል፣

4. የውሃ አገልግሎት ዓለማ ግቡን አንዲመታ የገጠረ መጠጥ ውሃ አገልግሎት በሥር ርዓትና በተቀለጠፈ መንገድ የማከሄድ ኃላፊነት አለው፣

5. የኅብረተሰቡ አባላት በውሃው አገልግሎት አንዲጠቀሙ አስፈላጊውን ቅስቀሳ ማካ ሄድ፣ የቁተር ቤት፣ የውሃ ማደያ የመሰሉትን በንጽሕናና ደህንነት በመጠበቅ ዘላቂ አገልግሎት አንዲሰጡ ማድረግ፣

6. የውሃ ሽያጭ ገቢን በመሰብሰብ ለውሃው አገልግሎት ሥራ ማስኬጃ አንዲውል ማድረግ፣

7. በውሃ አገልግሎት ላይ የሚደርሰውን ችግር ወይም ብልሽት በአቅራቢያው ለሚገኘው መንግሥታዊ አካል ወይም ሌላ የሚመለከተው ሪፖርት በማድረግ የጋራ መፍትሄ መፈለግ፣

8. ለውሃ ለማት ግንባታ ሥራ አስፈላጊውን የነፃ ጉልበት፣ የአካባቢ ቁሳቁስ ከተ ቻለም የጥሬ ገንዘብ አስተዋጽኦ የሚደረገበት መንገድ መቀየስ፣ በዚህ ረገድ የሚደረገውን የሕዝብ ተሳትፎ ማስተባበር፣

.../

CCRDA

7.4 <u>በገጠር የመጠጥ ውሃ ግምገማ ወቅት ከኅብረተሰቡ የሚፈለግ ተሳትፎ</u>

በገጠር የተሰረ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች በኢኮኖሚና በሶሻል መስክ ያስከተለውን ለውጥ የቴክኖሎጂውን ተስማሚነት በመገምገም ያሉ ችግሮችን በመረዳት መፍትሄ ለመፈ ለግና ጠንካራ ጎኖችን በበለጠ ለማጠናከር የሚረዳ ከመሆኑም በላይ ሌሎች ተመሳሳይ የመጠጥ ውሃ ሥራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

በመሆኑም በግምገማ ወቅት የኅብረተሰቡ ተሳትፎ ዓይነትና መጠን:—

- የቴክኖሎጂውን ተስማሚነት በሚመለከት አስተያየት ይሰጣል፤
- በአዲሱ የመጠጥ ውሃ መገንቢት ምክንያት የተገኘውን የጤና ማሻሻል ወይም አለ መሻሻል ላይ ባለው ሁኔታ ላይ ቃሉን ያሰማል፤
- በአጠቃቀሙ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ይገለፀልና፤
- በውሃ ፍለጋ ይጠፋ የነበረውን ጊዜ በመቆጠቡ የተገኘ የምርት ለውጥና በውሃ ፕሮጀክቱ ምክንያት የተገኙ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ፤
- መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማሻሻልና ለተፈጠረ አነስተኛ ችግሮች መፍትሄ የመሻት ጥረቶችን ያስረዳል፤
- ኅብረተሰቡ በየደረጃው ሁለገብ ተሳትፎ ማድረግ በሕዝቡ ላይ ያሳደረውን የባለ ቤትነትና በራስ የመተማመን ስሜት ለማወቅ በሚደረገው የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታ በመገምገም፤ አስተያየቶችን በመሰጠት ለሚከሄደው ግምገማ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል::

## 8. <u>በገጠር መጠጥ ውሃ ለማት የኅብረተሰብ ተሳትፎ የአሠራር ስለት (Implementation Procedures)</u>

የኅብረተሰብ ተሳትፎ ሥራ ዓይነቱ፤ መጠኑና ባሕሪው የተለያዩና የተወሳሰቡ (various and complex) ከመሆናቸው የተነሳ አንድ ወጥ የሆነ የአሠራር ስለት በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ሁኔታዎች አንፃር በሚከተሉት የአሠራር ስለቶች በመጠቀም በገጠር መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች "ራስን በራስ መርዳት" በሚለ መርህ መሠረት የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ተሳትፎ ማንቀሳቀስ ይቻላል::

.../

CCRDA

1. ድርጅታዊ መዋቅር በመዘርጋት፤

- የነብረተሰብ ተሳትፍን ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል አካለ ወይም ክፍል ከለ ማጠናከር ከሌለም ማዋቀር ይበጃል፤
- የነብረተሰብ ተሳትፍ ማዋቀር በዋና መ/ቤት ብቻ ሳይወሰን በየዘናትና በየወረ ዳዎች አንዲናር ማድረግ፤
- የውሃ ችግር የጠናባቸው የገጠረ ነብረተሰብ በየቂያቸው (በየመንደራቸው) የውሃ እና የጤና ኮሚቲዎች በማቋቋም በአቅራቢያቸው ከሚገኙ የወረዳ ነብረተሰብ ተሳት አደራጅ ጋር ግንኙነት አንዲፈጥረ ማድረግ፤ የወረዳው ለዘኔ፤ የዘኑም ለክለሉ በነብረተሰብ ተሳትፍ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የሥራ ግንኙነት መፍጠር...

2. የሥራ መመሪያዎችን፤ ደንቦችን ቅጾችን ማዘጋጀት፤

- በገጠር ውሃ ሥራ የነብረተሰብ ተሳትፍ የሚመሠረትበትና የሚሠራበት መመሪያ፤
- የውሃና የጤና ኮሚቴ ማቋቋሚያ መመሪያ፤
- የነብረተሰብ ተሳትፍ የፕሮጀክት ርክክብ ሰነድ፤
- መንግሥታዊና የውጭ አርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የፕሮጀክት ስምምነት እና የርክክብ ሰነድ፤
- የተለያዩ የነብረተሰብ ተሳትፍ የሥራ ማከናወኛና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾች::

3. ሥ ለ ጠ ና (Training) ፤

3.1 በመንደር ደረጃ

- ለውሃ ኮሚቴዎች የሚሰጥ ሥለጠና (የአስተዳደርና የሂሣብ አያያዝ)፤
- ለቀተር አንፈተርችና ለአደጅ ፓምፕ ኪርቴከርችን ማሠልጠን::

3.2 በቢሮ ደረጃ

- በረዳት ነብረተሰብ ተሳትፍ አደራጆችን ማሠልጠን፤
- በአገር ውስጥና በውጭ አገር የአጭር ጊዜ ሥለጠና ለባለሙያዎች መሰጠት
- ዓውደ ጥናት፤ ሲምፖዚየም፤ የአገር ውስጥና የውጭ የሥራ ገብኝት::

.../

CCRDA

4. <u>ሥራዎችን ማቀድና መምራት እንዲሁም መቆጣጠርና መገምገም፤</u>

የኅብረተሰብ ተሳትፎ ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ የተቀየሱ የአሠራር ስልቶች መሠረት ዕቅድ ማውጣት ተግባራዊነቱንም መከታተልና መቆጣጠር እንደዚሁም ወቅታዊ ግምገማ ማካሄድ፤ በዚህም መሠረት:—

- ሕዝብ ማስተባበርና ማደራጀት፤ ለገጠር የመጠጥ ውሃ ሥራዎች ማነሳሳት፤
- የገጠር መጠጥ ውሃን ለማለማት ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃ መሰብሰብ፤
- የውሃና የጤና ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ለሥራው የሰምምነት ስነዬችን መፈረም፤
- የውሃ አያያዝ፤ አጠቃቀምና የአካባቢ ጤና ትምህርት መስጠት፤
- ለቀተር ኦፕሬተሮችና ለአጅ ፓምፕ ኬር ቴክሮች ተገቢ ሥልጠና መስጠት፤
- ለውሃ ኮሚቴዎችና ሰለኮሚቴ ሥራ አስተዳደርና ሂሣብ አያያዝ ማስተማር፤
- ተገቢውን ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ያለመሰለቸት ማካሄድ፤
- የኅብረተሰብ ተሳትፎ ሥራዎችን የሚመለከት ሌሎች ተግባሮች መረዳም::

9. <u>የኅብረተሰብ ተሳትፎ የሥራ አንቅስቃሴዎችን የሚገድቡ ችግሮችና ዕንቅፋቶች (Limitations, Problems and Constraints)</u>

በታዳጊ አገሮች ውስጥ ችግሮች በየርዘን ይገኛሉ:: በዚህ የኅብረተሰብ ተሳትፎ ችግ ግሮችም በርካታ ናቸው:: የኅብረተሰብ ተሳትፎ አንቅስቃሴ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ በቢሮና በመስክ ደረጃ ሥራዎቹን የሚገድቡ አያሌ ችግሮችና አንቅፋቶች አሉ:: ከእነዚህም እንዳንዴቹ የሚከተሉት ናቸው::

9.1 <u>በቢሮ ደረጃ</u>

ሀ. ስለኅብረተሰብ ተሳትፎ ጽንሰኃሣብ በቂ ግንዛቤ ያለመኖርና ለሥራው ተገቢ ትኩረት አለመስጠት፤ ይህም በሥራው ላይ መጋተትንና ድክመትን ሲያስከትል በሠ ራተኞቹም ላይ የቀራለ ውድቀት አስከትሏል:: ለዚህ ችግር መፍትሔ በዐውደ ጥናት፤ በሲምፖዚየም፤ የመስክ ሥራ ጉብኝት በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የኅብረተሰብ ተሳትፎን ሥራዎች በማየት ለማቃለል ይቻላል::

.../

CCRDA

ለ. የኅብረተሰብ ተሳትፍ ሥራዎች በርካታና ውስብስብ የመስክ ሥራዎች በመሆናቸው በቂ የመገለገያ ቁሳቁስና የትራንስፖርት አቅርቦት ይጠይቃል:: የአነዚህ ተሟ ለተው አለመገኘት በሥራውና በሠራተኖቹ ላይ ተፅዕና ይፈጥራል::

ሐ. በኅብረተሰብ ተሳትፍ ሥራዎች ላይ በተሠማሩት በራሱ በኅብረተሰቡ፤ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች መካከለ የመረጻ ለውውጥ፤ የሥራ ግንኙነት፤ ቅንጅታዊ አሠራር፤ የሥራዎች መደራረብ፤ የሀብት ብክነት ... ወዘተ ችግሮች አስከትሏል::

መ. የሠለጠነ አና በቂ የሥራ ልምድ ያለው የኅብረተሰብ ተሳትፍ አደራጆች በብቃትና በጥራት ያለመገኘት የሥራውን አንቅስቃሴ አጓትቷል::

ሠ. የውሃ ችግርና ጪና ከወንጀች ይለቅ ሲቶችን የሚመለከት ሆና ሳለ በባሕሊዊ ተፅዕና ምክንያት ያለው አናሳ የሲቶች ተሳትፍ በሥራው ላይ ተፅዕና አስከትሏል:: በአደራጅነትና በውሃ ኮሚቴ አባልነት የሴቶች ተሳትፍ ከለተሻሻለና ከለተጠናከረ የገጠር የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ዓለማ ገቡን ሊመታ አይችልም:: በመሆኑም ችግር ለማቃለል የሲቶች ተሳትፍ መታከለ ይናርበታል::

9.2 <u>በመስኩ የኅብረተሰብ ተሳትፍ ሥራ ላይ የተከሰቱ ችግሮች፤</u>

ሀ. በራሱ በኅብረተሰቡ፤ በግለ፤ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች መካከለ የሥራ ቅንጅት (co-ordination) የመረጻ ለውውጥ በለመናረ ምክንያት የገጠረ የውሃ ፕሮጀክት ስታንዳርዱን (standard) ሳይጠብቅ በተስማሚ ተስማሚ ቴክናሎጂ (appropriate technology) ሳይመርጥ በርካታ የሰው ጉለበትና የሀገር ሀብት ፈሰበት የተሠረ ፕሮጀክቶች ጥቅም አለባ ሆነዋል:: ይህንን ችግር ለመፍታት ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን ያስፈለጋል::

ለ. የመስክ ሠራተኖች የሙያ ብቃት፤ የአቀራረብ ማነስ፤ በተለያዩ ምክንያቶች የሥራ ፍላጉት ማጧትና የአሠራር ጉድለት መፍጠር::

.../

CCRDA

ሸ. ለገጠሩ የውሃ ኘሮጀክቶች የመለዋወጫ ዕቃያች አጥረትና ጠርሶ አለመገኘት የጥ
ገናውን ሥራ አዘንፍታል:: የጥገና ሥራ በመዘግየቱና አንዳንዴም ጠርሶ ባለመ
ሠራቱ ኅብረተሰቡ በአሠሪው ድርጅትና መንግሥት ላይ አምነት አንዳይኖረው ሊያ
ደርግ ይችላል:: ይህ ችግር አንዲፈታ መንግሥት ወይም ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች
ለሠሩት የገጠር መጠጥ ውሃ ኘሮጀክት ጥገናን ችላ ሰይሉ በአፋጣኝ የሚሠራበትን
መንገድ ቢፈልጉ ችግሩ ይቃለላል::

መ. ለገጠሩ የመጠጥ ውሃ ኮሚቴያች ስለአስተዳደርና ሂሣብ አያያዝ ትምህርት ለአን
ረተርችና ለኬር ቴከርች (Operators and Care-takers)
ተገቢ ሥልጠና አለመስጠቱ በሥራው ላይ ችግር ፈጥርአል:: ይህንን ችግር ተገቢ
ሥልጠና በመስጠት ማቃለል ይገባል::

## ግ ጠ ቃ ለ ያ

ግንኛውም የልማት ሥራ በተለይ የገጠር መጠጥ ውሃ ኘሮጀክት ራሱን የቻለ በርካታ ችግርችና ውስብስብ ፀባይ ሰላለው የጥናቱ፤ የዕቅዱ፤ የግንቢታው፤ የአስተዳደሩ፤ የጥገናውና የግምገማው ሁኔታያችና ሂደቶች በጥንቃቄ መታየት አለባቸው:: ኘሮጀክቶቹ ከጥንሰሰ ጀምሮ አስከ ፍፃሜው የሕዝቡን ፍላጉት፤ አቅም፤ ባሕል፤ በጥቅሉ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ሁኔታያችን አገናዝቦ በቅንጅታዊ አሠራር መሠራት ይኖርበታል::

በገጠር የመጠጥ ውሃ ሥራያች ላይ ሰኪታማ ውጤት ለማግኘት የኅብረተሰብ ተሳትፍ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ታውቆና ተጠናክሮ አንዲሠራበት ማድረጉ ይበጃል:: በሰው ኃይል ሥልጠና በኩልም ከገጠሩ ነዋሪያች መካከል ቀላል የሆኑ ብልሽቶች በውሃ ተቋሞች ላይ ሲያጋጥሙ መጠገን የሚያስችላቸውን ያህል ዕውቀት የሚያሰገኝ ቀላል ሥልጠና መሰጠት ይጠቅማል:: ሌላው ተደጋጋፊና በጣም አስፈላጊ የሆነው የተሰማሚ ቴክኖሎጂ ጉዳይ ነው:: አንድን የውሃ ቴክኖሎጂ ለገጠሩ ሕዝብ ለማስተዋወቅና ብሎም ተጠቃሚው ሕዝብ በቀላሉ ተቀብሉትና ተደርድቶት በጥንቃቄ አንዲይዘው ከኢኮኖሚ አቅሙ፤ ከዕውቀት ደረጃው፤ ወዘተ... ጋር ማመጣጠን ያስፈልጋል:: በመሆኑም የኅብረተሰብ ተሳትፍ የሥራ አንቅስቃሴን ለማጠናከር የሚከተሉትን የና የና ተግባራት ማከናወን ይገባል::

.../

CCRDA

ቁጥጥርና ገምገማ

# MONITORING AND EVALUATION

በገጠር የመጠጥ ውሃ ፓምፖች አጋረሽን ፕሮግራም

ሥልጠና ዝርገራም ላይ የቀረበ

Presentation on the Training Programme for

Village Level Operation and Maintenance

of Pumps

CCRDA

## ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ

1. ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ምንድን ናቸው?

የክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ምንነት በዝርዝር ከማየታችን በፊት ፅንሰኃሳባቸውንበአጭሩ ለማ የት እንሞክራለን::

1.1 ክትትል (Follow-up)

አንድ ነገር ወይም ድርጊት ከጅምሩ አንዲት አንደሆነ የት አንደደረሰ በጥሞና ማወቅ መከታተልና የድርጊቱ ዓላማ አንዳይቃረጥ ሁኔታዎችን አመቻችቶ አገቡ አንዲደርስ ለማ ስቻል ነው:: ክትትል (Follow-up) የሚለው ቃል ከዌብስተር የአንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት (Webster English Dictionary defines follow-up is "Action in support of earlier action, pertaining to supplimentary action") ለረጅም ድርጊት የሚደረገው ድጋፍ፣ ለቀጣ ይነት የሚረዳ ተጨማሪ ኃላፊ ማለት ነው:: ስለዚህ ክትትል በተለይ የታቀደውን ኘሮ ጀክት በአቅዱ መሠረት በተመደበው ወጪ፣ በተሰጠው ጊዜና በተፈለገው መንገድ ተግባራዊ አንዲሆን ለማስቻል ለሥራ ሂደት መከታተያ የሚደረገው የአሠራር ስለት ነው::

1.2 ቁጥጥር (Monitoring, warning notice, caution)

አንድ ሥራ ወይም ኘሮጀክት በአቅዱ መሠረት በተሰጠው ጊዜና በተፈለገ መንገድ ተገባ ራዊ አንዲሆን ለማድረግ በወቅቱ የሚከሰቱ ችግሮችን በማወቅ የአርምት አርምጃ ለመው ሰድ የሚያስችል በሥራ ሂደት ወይም በኘሮጀክት አፈፀፀም ወቅት የሚከሄድ ለማኔጅመንት ውሣኔ አሰጣጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የአሠራር ስለት ነው::

1.3 ግምገማ (Evaluation - value determination, appraisal)

ግምገማ ከለፈው ኘሮጀክት የሥራ ለምድ የምናገኛቸው ጠንካራና ደክማ ጐኖች የመማሪያና የተገኘውን ለምድ የወደፊት ኘሮጀክቶችን በተሻለ መለክ ለማቀድና ለማዘጋጀት ወይም አገለግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ኘሮጀክቶችን አጠቃቀምና ያስከተሉትን ተፅዕና በማ ጥናት የሚሻሻሉበትን መንገድ ለመፈለግ የሚያስችል የአሠራር ዘዴ ነው:: ይህም የተነ

.../

CCRDA

ደፈ አቅድ ገብ መምታትና አለመምታት የወጪ ወጪን፤ የሰው ኃይልን፤ የመዋዕለ ንዋይ አጠቃቀምንና ሌሎች የሥራ ሂደቶች ሁኔታን ጠምሮ ይመረምራል፤ ያጤናል፤ ያስታውሳል፤ በአጠቃላይ ይገመግማል ማለት ነው::

ግምገማ ለኘሮጀክት ሂደት የሚከሄድ ቢሆንም አብዛኛው ኘሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከሄደ ነው:: ግምገማ የታቀደውንና የተከናወነውን አጉልቶ ለማነፃፀር ጥቅሙንና ጉዳቱን ወይም ትርፉንና ኪሣራውን ወይም ወጪውንና ገቢውን ለመረዳት ያስችላል::

2. ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ

አንድ ኘሮጀክት በምናቅድበት ጊዜ በተፈለገው ሁኔታ ዕቅዱን ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስለት ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ በመሆኑ አንደአንድ የኘሮጀክት አካል ተወስዶ ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ምቼ? በማን? ለምን? እንዴት? የሚሉት ኃሣቦች አብረው በኘሮጀክቱ አቅድ ሊካተቱ ይገባል:: ክትትል ከግምገማ ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በተለይ የታቀደው ኘሮጀክት በአቅዱ መሠረት መከሄዱን በየወቅቱ ተከታትሎ ጤናማ የሥራ ሂደቱን ለማበርታት በተሻለ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማስቻልና ስህተትን ወይም ለዩ ለዩ ችግሮች ቢከሰቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል:: በሌላ አንፃር ክትትልና ቁጥጥር በየወቅቱ የሚደረግ አነስተኛ ግምገማ (Mini Evaluation) ነው:: አብዩ ወይም ዋናው ግምገማ ግን ከላይ እንደተመለከትነው አብዛኛው ኘሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከሄድ ነው::

2.1 የግምገማ ዓይነቶች

ለተለያዩ ዓለማ በተለያዩ ጊዜ፤ በተለያዩ ሰዎች የሚከሄድ አራት ዓይነት የግምገማ ሂደቶች አሉ::

2.1.1 ቅድመ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ (Preliminary Evaluation

ይህ የግምገማ ዓይነት በዕቅድ(Planning) ወቅት የሚደረግ ነው:: የኘሮጀክቱ ዓለማ ለኘሮጀክቱ መሰከት አንቅፋት ሊሆኑ የማችሉ ነገሮች፤ ስትራቴጂዎች፤ ፖሊሲዎች፤ ድርጅታዊ መዋቅር፤ ማኔጅመንትና ሌሎች ለኘሮጀክቱ ሥራ ሂደት ስኬታማነት የሚረዱ ጉዳዮችን የምንዳስሰበት ደረጃ ነው:: የዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ዓለማም የተነደፈው የኘሮጀክት ዕቅድ በወቅቱ ሁኔታ ግለትም ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሠ

.../

ረተና ተገቢራዊ ሊሆን የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥና ለዩነቶች ወይም ችግ
ሮች ካሉ የኘሮጀክቱ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለማስተካከለ መቻል ነው::

2.1.2 በየወቅቱ የሚደረግ ግምገማ (Periodical Evaluation)
የዚህ ዓይነቱ ግምገማ ኘሮጀክቱ በመካሄድ ላይ አያሉ የሚደረግ ሲሆን ጊዜው
አንደአስፈላጊነቱ በኘሮጀክቱ ሁኔታ በወር ወይም በረብ ዓመት ወይም በመንፈቅ
ለወሲን ይችላለ:: ዓላማው ስለኘሮጀክቱ አፈፀፀም ሂደት መረጃ ለማግኘትና
ምን ደረጃ ላይ አንደደረሰ የተፈለገውን መንገድ የተከተለና ያለተከተለ
መሆኑን በማወቅ ለጋጠሙ ችግሮች መፍትሄ በመፈለግ ኘሮጀክቱ በአቅዱ መሠረት
አንዲቀጥል ማድረግ ነው::

2.1.3 ከኘሮጀክት ፍፃሜ በኋላ የሚደረግ ግምገማ (Post Evaluation)
ይህ የግምገማ ዓይነት የኘሮጀክቱ ሥራ ከተፈጸመ በኋላ የሚደረግ ሲሆን
የኘሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ኘሮጀክቱን አንዴት አንደተቀበሉትና የወደት ሁኔታ
ምን ሊሆን አንደሚችል ትኩረት የሚሰጥ ነው::

2.1.4 በኘሮጀክቱ መሠረት የመጪ ወይም ሊመጪ የሚችል ግምገማ(Impact Evaluation)
በዚህ ግምገማ ወቅት ኘሮጀክቱ በተጠቃሚው ሕዝብ ላይ ያመጪው ለውጥ ምን
አንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል ነው:: ለውጡ ጠቃሚ (Positive)
ወይም ጉጂ(Negative) ሊሆን ይችላል:: ለውጡም ኢኮኖሚያዊ፤ ማሕበራዊ
ወይም ፖለቲካዊ ሊሆን ይችላል:: የዚህ ዓይነቱ ግምገማ በአብዛኛው ኘሮ
ጀክቱ ከተጠናቀቀና አገለግሎት መስጠት ከተጀመረ በኋላ ነው:: ኘሮጀክቱ
ከመጀመሩ በፊትም ጠቃሚና ጉጂ ሁኔታዎች ጥቅሙና ጉዳቱን በማነፃፀር ተገ
ምገሙ ጥቅማጥቅሞቹ የሚያድጉበትና ጉዳቶቹ ገን የሚወገዱበት ወይም የሚሸሸ
ለፀት ሁኔታዎች በአጥኚ ምሁራን በቅድሚያ ተገምግሙ ይጠቆማል::

3. በክትትል፤ በቁጥጥርና በግምገማ ለተረጋገጡ ችግሮች የመፍትሔ ነጥቦች፤

የኘሮጀክቱን የሥራ ሂደት ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ በማድረግ የችግሮቹን መንስኤ በማሰፈር
ብቻ ችግሮቹ ሊፈቱ አይችሉም:: ስለዚህ ለችግሮቹ የመፍትሄ ኃሣቦችም ከዚህ በታች በተመለከቱት
ነጥቦች መሠረት መቅረብ አለባቸው::

..../

CGRDA

- አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች አገልግሎት አንዲሰጡ የሚደረጉበት መንገድ፤
- አገልግሎት የሚሰጡ ፕሮጀክቶች ይበልጥ የሚሻሻሉበት፤
- የፕሮጀክት አጠቃቀምና አያያዝ የሚሻሻልበት ሁኔታ፤
- ጉን ለጉን አብሮ መሄድ የሚገባቸው ሌሎች ፕሮጀክቶች ከሉ የመጠቀም ወይም አንደገና ትኩረት የመስጠት፤
- ወደፊት የሚታቀዱ ፕሮጀክቶች የሚሻሻሉበትን መንገድ፤
- ከአንድ ፕሮጀክት አፈፀፀም የተገኘው ልምድ ለሌሎች የሚተላለፍበትን መንገድ መቀየስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

4. ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ በማን ይከሃዳል?

ከዚህ በታች በተገለጹት በሦስት በተለያዩ አከላት ይከሃዳል::

- በፕሮጀክቱ ሰዎች፤
- ከፕሮጀክት ወጪ ባሉ ሰዎች አና
- ሁለቱ በጋራ በመሆን የሚያከሂዱት ነው::


ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ የሚያከሂዱ ሰዎች የተለያዩ በመሆኑ ቁጥር የግምገማው ዓለማም የተለያየ ሊሆን ይችላል:: ከፕሮጀክቱ ወጪ ባሉ ሰዎች የሚደረግ ግምገማ በአብዛኛው የገንዘብ ወጪውን ከሚሸፍኑ ድርጅቶች (አርዳታ ወይም ብድር ሊሆን ይችላል::) የወጪውን ገንዘብ ምን ላይ አንደዋለ ለማወቅና የሚቀጥለውን ገንዘብ ለመፍቀድና ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ነው:: በፕሮጀክቱ ሰዎች የሚደረገው ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ግን ሥራው በትክክለ አንዲከናወን ገንቢ የሆኑ ኃሳቦችን ለማነጅመነት ግቅረብና ለውሣኔ አሰጣጥ አመቺ አንዲሆን ማድረግ ነው:: በሁለቱም በጋራ የሚደረግ ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ደግሞ ለሁለቱ የጋራ ዓለማ የሚደረግ ነው:: ግምገማው በወጪ ኤክስፐርት፤ በህብረተሰቡ፤ በፕሮጀክቱ ሠራተኖና አስተባባሪ ሊከሃድ ይችላል::

5. የግምገማ፤ የክትትልና የቁጥጥር ደረጃዎች

የፕሮጀክት ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ደረጃዎች የአሠራር ስለተቹን ከሚከተለው ቻርት አንመለከ

.../

CCRDA




6. የፕሮጀክቱ ዓለማና ግብ ጠቃሚ ነጥቦች:—

በአንድ የመጠጥና የአካባቢ የጤና ፕሮጀክት የገምገማ ወይም የክትትል ሥራ ለማካሄድ ጠቃሚ ነጥቦች የሚፈለግ መረጃ የመረጃ አሰባሰቡ መንገድና የሚፈለገው ገንዘብ ጠቃሚዎች ሲሆኑ የፕሮ ርጀክቱን ዓለማና ግቦች (Project objectives and goals) ለይቶ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው:: የፕሮጀክቱ ዓለማ ማወቅ ማለት ፕሮጀክቱ

| | | |
|---|---|---|
| ለማን? | who? | አንደተሠራ ማወቅ ማለት ነው:: |
| በምን? | what? | |
| እንዴት? | how? | |
| መቼ? | when? | |
| ለምን? | why? | |

ይህ ደግሞ በሌላ መለኩ ገምገማ በሚካሄድበት ወቅት ፕሮጀክቱ በታቀደው መሠረት ለመከናወኑና የታለመውን ውጤት ማስገኘቱን ለማነፃፀር ወይም ለማወዳደር ዓይነተኛ ድርሻ አለው::

በዚህ መሠረት የአንድን የመጠጥ ውሃና የጤና ፕሮጀክት ዓለማዎች ጠቃሚ ነጥቦች፤ የሚፈለጉ መረ ጃዎችና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን እንደሚከተለው እናሳያለን::

.../

CCRDA

የአንዱ የመጠጥ ውሃና የአካባቢ ጤና ኘሮጀክት የረጅም ጊዜ ዓላማ /ግብ/ በጥቅሉ የማያቋርጥ የውሃ፣ የጤና አገልግሎት አንዲናር በማድረግ የኘሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚሆነውን ወይም የሆነውን የሕዝብ የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ ደህንነት ዋስትና፣ የማሪት አቅምና አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ነው:: As it has been indicated, on PROWWESS publication of September 1990, Taking the Pulse for Community Management in Water and Sanitation which reads, "Installation of water and sanitation facilities is not an end in itself, but a means to improve health and productivity and a better living environment." through acheiving the three overriding goals and objectives of water supply and sanitation project which are sustainability, effective use and areplicability, there by reach to capacity building according to the following illustrations: The three measurable goals of objectives of water sector strategies for community are:

| Goals and Objectives | Elements and Indicates |
|---|---|
| i) Sustainability | |
| - Functioning systems ..... | Quality of water at source<br>number of facilities functioning break down and repairs. |
| - Management and capacity building | |
| . Individuals ..... | Management abilities (decision making), knowledge and skills confidence, self concept. |
| . Local Institution ... | Autonomy<br>Supportive leadership<br>system for learning and problem solving. |
| . Financing and cost sharing ..... | Community contribution<br>Agency contribution<br>Unit cost |

.../

CCRDA

ii. Effective use

| | |
|---|---|
| - Optional use ..... | Number and characterstics of users<br>Quantity of water used all purposes<br>time taken to use facilities.<br>Management of water resource. |
| - Hyginic use ..... | Water quality at home.<br>Water transport and storage practice.<br>Home practice to improve water quality site and home cleanliness.<br>Personal hygine. |
| - Consistent use ..... | Pattern of daily use<br>Pattern of seasonal use. |

iii. Replicability

| | |
|---|---|
| - Community ability to expand services ..... | Additional water (laterine) facilities build by community up-grounding of existing facilities.<br>New development activities undertaken. |
| - Transfer ability of agency Methods and Strategies ... | Proportion and role of specialized personnel.<br>Established institutional frame-work. Budget size and sheltering.<br>Documented planning and implement initiation procedures. |

- Sustainability:- is achieved through building local capacity to anticipated and solve problem as it arises. At a minimum it implies community and agency capacity to keep systems functioning.


- Effective use:- is optimal, hyginic and consistent use of water and sanitation facilities so as to maximize benefit and minimize negative consequences over an extended period of time. Since woemn are the primary users focus on their participation, ensure their integration. Effective use is only acheived when people accept new practices and make them part of their evey day behaviour.

.../

CCRDA

- Replicability:- at the community level means that users acheived such a high degree of self-confidence and sufficiency that they can expand their efforts to new areas. For the sector agency, replicability means that elements of successful methods and approaches can be transferred to the other projects/programs or new geographical areas.

In practices, there is a considerable overlap amont this three goals and objectives. In particular, capacity-building within the community is the main requirement for progress towards all three goals as seen from the diagram below:




To ensure inclusion of women and their improvement in the quality of lives, gender analysis are essential throughout monitoring and evaluation of water supply and sanitation project.

የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ዓላማዎችና ግቦች ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፡

- ፕሮጀክቱ ግለጋሉት የሚሰጥ (Effective use)
- ዘላቂነት (Sustainability)
- ተጠቃሚው በትክክለና በበቂ ሁኔታ በመጠቀም አምሰያውን ወደሌላ አካባቢዎች ሲያስፋፋ (Replicability) ሲሆን ነው::

6.1 የፕሮጀክት ዘላቂነት (Project sustainability) ማለኪያ

የፕሮጀክትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ከሁሉም በላይ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ክትትል፡ ቁጥጥርና ግምገማ የሚያሻ ሲሆን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የአርዳታ ሰጪዎች ድጋፍ ትብብር ያስፈልጋል:: ዘላቂነት (Sustainability) የገንዘብ፡ የአስተዳደርና የለዩ ለዩ ቴክኒካዊ አርዳታዎች ከተቋረጠ በኋላ ቢሆን በተጋዳኝ ድርጅትና ነብረተሰብ በጋራ የተገኙትን ጥቅሞችና ጥረቶች የአካባቢውን ሁኔታ በማይጉዳ መንገድ አንደተጠበቁ አንዲቆዩ ማድረግ ነው:: ወይም ዘላቂ ማለት የተሠራውን ፕሮጀክት በበቂ ሁኔታ ያለማቋረጥ ግለጋሉት አንዲሰጥ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ማለት ነው:: ማኛውም ነብረተሰብ

.../

CCRDA

ግንኛውም ኅብረተሰብ በአለበት የሚቆይ አይደለም:: ሁልጊዜ በአንቅስቃሴና በለውጥ ሂደት ውስጥ ነው:: የተሠረ ሥራዎችም ወይም ፕርጀክቶችም ከዚህ አንደገና አየተለወጠ ከሚሄደው ኅብረተሰብ ጋር መጣጣም አለባቸው:: በመሆኑም ፕርጀክቱ ዘላቂ አንዲሆንና ችገርች በሚናሪበት ጊዜም መፍትሔ የሚፈለግ:—

- በተጠቃሚው ኅብረተሰብ (Beneficiary community)
- ክመንግሥት (Government)
- በተጓዳኛ የአርዳታ ሰጪ ድርጅት (Assisting NGO)

በኩል ችገርችን ለመፍታት የሚያስችል አቅም (problem sovling capacity) መዳበር ይኖርበታል:: ለዚህ ጉዳይ ተግባራዊነት ቀናውና አንዱ፤

- በራሱ በተጠቃሚው ሕዝብ
- በአካባቢው መንግሥት አካል
- በአርዳታ ሰጪ ድርጅት

} በኩል የሰው ኃይል የሚቴሪያል፤ የመዋዕለ ንዋይ

አቅምን ማጠናከርና ማሳደግ አስፈላጊ ነው::

የኅብረተሰቡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት (Community decision making process which is part and parcel of community empowerment ) መሰተፍ ለፕርጀክቱ ዘላቂነት ወሳኝ ነው:: ኅብረተሰቡ በወሳኝነትና በሥልጣን ባለቤትነት (Communities decision empowrment) የሚሰተፍበት አሠራር የሕዝቡን በራስ መተማመን፤ በአስተዳደርና ጥገና ያለውን ብቃት አውቅትና አዲስ ኃላፊነት የሚፍለቅ ችሎታውን ያዳብራል:: በአርገጥ ደህና አንዲሆን ደግሞ የለውጥ ሰዋርያ የመሣርና ችገርን በጋራ የመፍታት ድጋፍ የመስጠት ችሎታ ባላቸው የሚኔጅመንት ሰያች መጠቀም አስፈላጊ ነው:: በአጠቃላይ የፕርጀክትን ዘላቂነት ለመከታተል፤ ለመቆጣጠርና ለመገምገም ቁልፍ የኅብረተሰቡን አስተዳደርና ሥልጣን (Community management and empowerment) በሚጠናከርና በመንግሥትና በአርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ትብብርና ድጋፍ መታቀፍ ወሳኝ ነው::

6.2 አገለገሉት የሚሰጡ ተቋማት ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ (Functioning systems effective use follow-up, monitoring and evaluation) በፕርጀክት አስተዳደር ወቅት የሚደረገ የኅብረተሰብ ተሰተፍ ከሚነፀባረቅበት አንዱ መን ገድ ፕርጀክቱ ያለምንም ማቋረጥ ገለጋሉት አንዲሰጥ ማድረግ ነው:: ይህ ጥረት ደግሞ

.../

CCRDA

የኅብረተሰቡን የገንዘብ አቅምንና ፍላጐትን የሚወሥር ነው:: ለዚህም የናው ወሰኙ መንገድ ኅብረተሰቡ የበለቤትነት ስሜት እንዲድርበት በዕቅድ አወጣጥና አፈ ፀፀም ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፍ ግድረግ ነው:: በአርገጥ ይህ ግለት ደገሙ ኅብረ ተሰቡ ሁሉን ነገር በራሱ ይወጪል ግለት አይደለም:: ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥሙ የመንግሥትንና የውጭ አርዳታ ሰጪዎች ጠንካራ ድጋፍ ያሰፈልጋል:: አገ ለግሎት በሚሰጠት ላይ ያሉት የውሃና የጤና ተቋማት በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች መከታተለ፤ መቆጣጠርና መገምገም ይቻላል::

አነሱም:— ሀ. የአገለግሎቱ መጠንና ጥራት (Service quantity and quality)

ለ. የብልሽት ጊዜና ጥገና (Break-down and repair)

ሐ. የወጪ አሸፋፈን ድርሻና የአያንዳንዱ ዋጋ (Cost sharing and unit costs)

ሀ. የአገለግሎት ወጪና ጥራት ግምገማ (Service quantity and quality evalua

ዓለማው፤ ተጠቃሚ ኅብረተሰብ ዓመቱን በሙሉ በብቃትና በጥራት የሚገለገልቸው ተቀባይነት ያላቸው የውሃ ጣቢያዎች ቁጥር አንዲወሥር ግድረግና አገለግሎትን ማዳራስ ነው::

<u>በዚህ ግምገማ ወቅት የሚፈለግ መረጃ፤</u>

- የተሸሸሉ የውሃ ጣቢያዎች ቁጥጥር መጨመርና አለመጨመር፤
- በየጊዜው አየጨመረ የሚሄደውን የሕዝብ ፍላጐት ለማሟላት የሚያስችል ከውሃ መገናኛዎች የተሸሸለ በቂ ውሃ ይገኛል ወይ? ለተለያዩ አገለግሎቶች አገለ ግሎቱና ተጠቃሚው ተመጣጣኝ ናቸው ወይ?
- የታቀደውና የተገኘው ውጤት አንዲት ነው?
- የሚገኘው ውሃ ጥራቱ ተቀባይነት አለው? ሽታው? ጣዕሙ? ቀለሙ? ...?
- ውሃው ከመገኛው የተጠበቀ መሆኑ ...? ንጽህና...?
- የሚፈለገውን ጥራት ይዟል ወይ? (who started of drinking water?)
- በበጋና በክረምት ያለው መጠን አንዲት ነው?
- የንጽህና ጉዳይ በቤት፤ በአንዳንድ ተቋማት በቂ ሽንት ቤቶች አሉ?
- የሽንትቤቶች ሁኔታ አንዲት ነው? አሠራረን? ሽታው? ...? ...? ...?

...

CCRDA

በምገማው ወቅት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

_ የመስክ ጉብኝት ማድረግ፤
_ በውሃ መገኛዎች (at water sources) የውሃ ጥራት ምርመራ ማድረግ፤
_ የውሃ ምርት መጠንን መለካት (ለአድ ፓምፕና በምንጭ በደቂቃ ወይም በሲከንድ የሚመረተውን ምርት መለካት፤)
_ የቴክኒክ ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ማድረግ፤

ለ. የውሃ ጣቢያ ስብራትና ጥገና ሁኔታ መገምገም (Break-down and repair evaluation)

ዓላማው፤ ነብረተሰቡ፤ መንግሥትና አርዳታ ሰጪ ድርጅት ግንባር በመፍጠር የውሃ ጣቢያ ብልሽት አንዲቀንስ ጥገና ሲያስፈልግና ብልሽት ሲያጋጥም በጋራ አፋጣኝ መፍትሔ ለማስገኘት ነው:: የውሃ ጣቢያዎች በምን ያህል ጊዜና አንዴት አንደ ሚሰበሩ ለጥገና የሚሰጠው አፋጣኝ ምላሽ፤ የቴክኒክ ሁኔታ ነብረተሰበ በጥገናና በአስተዳደር ያለው ችሎታ፤ የጥገና ወጪ፤ የመለዋወጫ አቃዎች መኖርና አለመኖር፤ ያለው የመንግሥት ድጋፍ፤ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ አርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ተሳትፎ፤ የቴክኖሎጂ ተስማሚነት ... (Is that VLOM types ...)

በዚህ ግምገማ ወቅት የሚፈለግ መረጃ፤

_ ጥገና የሚካሄደው በማን ነው?
_ ነብረተሰቡ በጥገናና በአስተዳደር የሥራ ድርሻ አለው? የሥራውን ድርሻ ያውቃል? ይህ የሥራ ድርሻው በወንዴቹም በሴቶቹም ተቀባይነት አለው?
_ የጥገናና የአስተዳደር ደንብ አሊቸው? ደንቡ በተግባር ላይ አየዋለ ነው?
_ የነብረተሰቡ አነስተኛ ወይም ከባድ ጥገናዎች ለማካሄድ ችሎታ አሊቸው?
_ ቴክኖሎጂው ከሕዝቡ ምርጫ፤ ባሕልና አቅም ጋር ተመጣጣኝ ነው?
_ የውሃ ጣቢያዎች ስብራት ድግግሞሽ (Frequency of break-down) አንዴት ነው? ከተሠራ ምን ያህል ጊዜ ተሰበረ? አፋጣኝ ጥገና ይደረጋል ወይ?
_ ነብረተሰቡ፤ ተጠቀሚው ከአቅም በላይ ለሆነ ብልሽት ለማን ሪፖርት ማድረግ አንዳለባቸው ያውቃሉ? የአስተዳደርና የጥገና ሥልጠና ተሰጥቷል?

.../

CCRDA

- የስለጠናች ምርጫ ተደርጋለ? የሥለጠና ጊዜ በቂ ነው? የሥለጠናው ቦታ ምቹ ነው?
- የጥገና መሣሪያያች ይገኛሉ? የመለዋወጫ አቃያችስ? ዋጋቸውስ?
- ከነብረተሰቡ/ከተጠቃሚው የመገዛት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ነው?
- ከተጠቃሚው ሕዝብ አቅም በላይ ለሆኑ ጥገናዎች ከመንግሥት ወይም ከአርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍ አለ? ካለ ድጋፉ በቂ ነው?
- በጥገና ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ምንድን ናቸው?

<u>በዚህ ምዕራፍ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ፡</u>

የመሰክ ዝቦች በማድረግ፡

- ከተጠቃሚው ነብረተሰብ ተወካዮች፡
- ከክለሉ ሹማምንቶች፡ ከውሃ ተገለጋዮች በተለይ ከውሃው ቀጂ ሴቶችና ለጆች፡
- ከውሃና ጤና ኮሚቴዎችና ከኬርተከርች (Care-takers) ጋር ውይይት በማካሄድ፡

ሠ. ለጥገና የሚወጣ የወጪና የወጪ አሸፋፈን ሁኔታ፡

ዓለማው፡ የውሃ ወይም የጤና ፕሮጀክቶች አገለገሉት ወጪ የአስተዳደርና የጥገና ጠምሮ፡

- በተጠቃሚ ነብረተሰብ
- በመንግሥት
- በውጪ አርዳታ ድርጅት
- በግለሰቦች
- በሌሎች ወይም በጋራ

ሊሸፈን የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ::

<u>የሚፈለግ መረጃ</u>

- የፕሮጀክቱን አስተዳደርና ጥገና የሚሸፍነው ማነው?
- የተጠቃሚው ነብረተሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ ለአስተዳደርና ጥገና ወጪ መክፈል ይችላሉ? የመክፈል ፍላጉታቸውስ?
- የገንዘብ የገቢ ምንጭ የሚፈጥሩት አንዴት ነው? የቁጠባ ሥራዎች ሥራ በመሥ
- ለገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ያወጡት ደንብና መመሪያ አለ? ካለ በአግባቡ ይሰራበታል?

.../

CCRDA

<u>የዚህ የገምገማ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፤</u>

ገንዘብ ከሚከፍሉና ከማይከፍሉ፤ ክፍያ ከሚያስወስቡ፤ ከውሃና ከጤና ኮሚቴ አባላት ጋር ውይይት ማድረግ፤

- በሚሠራው (በውሃና በጤና) ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በመገኘት፤
- በየወራቱ ከተሰበሰበ የገቢ ሁኔታ በማጥናት::

6.3 ግለጋሎትን ለማስፋፋት የሰው ኃይል አቅምን ማሳደግ

(Human capacity development for service replicability)

ራስን መቻል ያለሰው ኃይል የሥራ አቅም መሻሻል ወጪ አይታሰብም:: ራስን መቻልና የሥራ ብቃት የሚዳብረው ደግሞ ሰዎች በአስተዳደርና በአደረጃጀት ለምድ አውቀት ሲያገኙና የራሳቸውን ዕውቀት ማመንጨት ሲችሉ ነው:: ሰዎች በተፈጥሮ ለዩ የማሰብ የማሰላሰልና ዕውቀትን የማመንጨት ችሎታ አላቸውና:: ስለኘሮጀክቱ ግለጋሎት ዘላቂነትና አምሳያውን ማስፋፋት (Project service sustainability and replicability) ከሰው የሥራ አቅም ገንቢታ ይመነጫል:: ለዚህም የመንግሥትና የወጪ አርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ድጋፍና ትብብርን ይሻል:: ይህንን ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችሉ ሦስት ጠቃሚ ነጥቦች አሉ:: አነሱም:—

- የማኔጅመንት ችሎታ ...?
- በቂ የሥራ ለምድና አውቀት ...?
- በራስ የመተማመን ሁኔታ በነብረተሰብ፤ በመንግሥትና በመንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች በኩል መኖረን ማረጋገጥ ነው::

ይህን ሁኔታ ለመገምገም ትንሽ አስቸጋሪ ቢሆንም በአዝቢቲ፤ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ነብረተሰቡን በማስተማር፤ በመቀስቀስና በማደራጀት በተለያዩ የኘሮጀክት ደረጃዎች የውሣኔ አሰጣጥና የሥራ አንቅስቃሴ ውስጥ ያደረገውን ተሳትፎ ማጥናት፤ የሰው የሥራ ኃይል አቅም ማደጉን አለማደጉን ለመረዳት ያስችሉናል::

<u>በዚህ ገምገማ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎች፤</u>

- የነብረተሰቡ ተሳትፎ በኘሮጀክቱ የሥራ ውሣኔ አሰጣጥ ምን ያህል ነው? ነበር? ከፍተኛ? መካከለኛ? ዝቅተኛ? በተለይ የሴቶች ተሳትፎ እንዴት ነው? ነበር?



CCRDA

- ችግርችን የጣወቅና የመለየት ችሎታስ?
- የቴክኖሎጂ ምርጫ፤ ዲዛይን፤ ዕቅድ አፈፃፀም፤
- የውሃ ጤቢያዎች ምርጫ? የውሃና የጤና ኮሚቴ ምርጫ? የሴቶች ተሳትፍ?
- ተጠቃሚው ኅብረተሰብ የመክፈል አቅም?
- ሕጉችና ደንቦችን የጣውጣት ችሎታ፤ የአሠራርና የጥገና ዘዲ? ወዘተ...
- ወንዶች፤ ሴቶችና ልዮች ያሊቸው አውቀት ችሎታ (Skill) በኘርዮክቱ የሥራ ግንባታ፤ አስተዳደር አኘረሽንና ጥገና ወቅት አንደሆነ ወይም አንደነበር መገምገም ይኖርበታል::
- ኅብረተሰቡ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አዲስ ሥራ ዎችን ለመሥራት ያለው ብቃትና ችሎታው አንዲት አንደሆነና ለወደፊቱ በዚህ ረገድ ለመሥራት ያለው ፍላጉት ...?
- የአካባቢው ተቋማት ብቃት (Local Insitutional Capacity) ከላይ በተመለከቱት ነጥቦች አጣኪይነት ሊገመገም ይገባል፤
- የቡድን መንፈስ መኖር ሥራዎችን በተዋረድ የመከፋፈልና የመቆጣጠር ተመሳሳይ መረጃ ዎችን መሰብሰብ አስፈላጊ ነው፤
- የቡድን አባላት የሚማሪበትንና ችግሮች በጋራ የሚፈቱበት ዘዲ (System for learning and problem solving) መኖር አለመኖሪን መረጃ ለውውጥ፤ በጋራ ውይይት ቀራኒዎች በመፍታት ራስን በመመርመር (Self diagnosis) ችግርችን በጣወቅና በጋራ ተመካክሮ የሚወዱበትን መንገድ በመቀየስ አንፂር ሊገመገም ይገባል፤
- በድርጅቶች መካከል ያለው ትብብርና ቅንጅታዊ አሠራር በአቅድ አወጣጥና አፈፃፀም፤ በአስተዳደርና ጥገና፤ በግምገማና ከትትል አንፂር መረጃዎች ሊጠናቀሪበት ያስፈለጋል

<u>በዚህ ግምገማ ሊያገለግል የሚችል የመረጃ አሰባሰብ ዘዲ፤</u>

- በግለና በቡድን ቃለመጠይቅና ምልለስ በጣካሄድ፤
- ከኮሚቴዎች ጋር የቡድን ውይይት በጣካሄድ፤
- የጽሑፍ መጠይቆችን በጣዘጋጀት፤ (Questionaire)
- የግለና የጋራ ምለከታ (Observation) በጣድረግ መረጃዎችን ግሰባሰብ ይቻላል::

.../

CCRDA

ከአዋጋቢ የገጦገጣ ወጪት አንፂር አንዳንድ ኘሮጀክት በአጦሰሉ ወደ ሌላ አካባቢ አንዲሰፋፋ ማድረግ፤

(Replicability)

አንድ ኘሮጀክት ሂደቱ ዋቅሙና አዋጋቢነቱ በአንድ አካባቢ ከታየ በኋላ በአጦሰሉ ወደሌላ አካ
ባቢ ለማዳረስ የኘሮጀክቱን ደረጃ ግየት አስፈላጊ ይሆናል:: በሙከራ ዋናት (pilot study)
ኘሮጀክቱ ከለው የአካባቢ ዕውቀትና ሁኔታ አኳያ በአጦሰሉ ወደሌላ ማስፋፋት(Replication)
ጦርትን፤ የአስተዳደር ችሎታን በሌሎች አንዲሰርጽ ለማድረግ የሰለጠነ የሰው ኃይል ይጠይቃል::
ኘሮጀክቱን በአጦሰሉ ወደሌላ ማስፋፋት በአካባቢው የሚገኘውን የጣቴሪያልና የሰው ኃይል በመጠቀም
የሚካሄድ ኘርገራጦ:—

_ በተለይጦ ለሙያው የሠለጠኑና ቴክናዊውን የሚያውቁ የአካባቢ ሰዎች መኖር፤

_ ኃላፊነት ያለውና የሥራ ክትትልና ቁጥጥር ገጦገጣ የሚያደርግ ድርጅት፤

_ የተመደበ በጀት፤

_ የአቅድና የአፈፀፀጦ ደንቦች መናር ግወቅ በጣም ጠቃሚ ነው::

በገጦገጣና ክትትል ወቅት የኅብረተሰብ ተሳትፍ ሚና ምንድን ነው?

የኘሮጀክቱ ዓለማ ገቡን መምታት አለመምታት በትክክል ለይቶ ለመነገር የሚችለው የታለመለት
ተጠቃሚ ኅብረተሰብ(The traget beneficiary community) ብቻ ነው:: በዚህ
መሠረት ተጠቀሚው ኅብረተሰብ ሊያደርግ የሚገባው:—

_ በመረጃ መሰብሰብ ተቀዳሚ ሚና መውሰድ ያሰፈልጋል፤

_ በገጦገጣና ክትትል ሥራ ላይ ከተሠማረ ሠራተኖች ጋር በመተባበር የሚጠየቀውንመረጃ
መሥጠት፤ መምከርና መጠቆም፤

_ ለኘሮጀክቱ መሻሻል የሚረዱ ገንቢ አስተያየቶችን በመሥጠት ከፍተኛ የሥራ ድርሻ አለው::

CCRDA

# ሻለ ሃምሳ

CCRDA

የኢትዮጵያ ወሳኝ ሥራዎች ኮሚሽንን ለማቋቋም በወጣው

አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፰/፲፱፻፸፩ ዓ.ም የተቋቋመ

የኢትዮጵያ ወሳኝ ሥራዎች ኮሚሽን ማቋቋሚያ

ደንብ ቁጥር ፭፻፸፱/፲፱፻፸፩

ደንብ ቁጥር ፭፻፸፱/፲፱፻፸፩

የኢትዮጵያ ወሳኝ ሥራዎች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ

ቁጥር ፭፻፸፱/፲፱፻፸፩ ዓ.ም

ሚያዝያ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም

አዲስ አበባ

CCRDA

ይህ መመርያ በኢትዮጵያ ውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የጥናትና ምርምር ቡድንና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኩኩልቲ ጉብብር በምርምር ካሉገኙ ሁለቱ የኣጅ ፓምፓች መሀለል አንዱን ይገልፃል ። በውስጡም ይኸን የኣጅ ፓምፕ ለመትከልና ለመጠገን የሚያስችል በሥዕል የተደገፌ መግለጫ ይዟል ።

የኣጅ ፓምፑ የሚጠቅመው ከመሬት ኣለከ ውሀው ድረስ ፬ ሜትር ያህል ጥልቀት ላላቸው የኣጅ ጉድጓዶች ውሀ ለማውጣ ነው። ኣለከ ፲፫ ሜትር ድረስ ቢተከል ግን ሌሎች ሀፃናት ውሀ ለማውጣት ይከ-ብዳቸዋል።


ይህ መመርያ ገና የመጀመሪያ ሙከራ ስመሆኑ ብዙ መሻሻል ያስፌልገዋል። ስለዚህ ተጠቃሚዎች ያሉቸውን የማሻሻያ ሀሣብ በሚቀጥለው ኣደራሻ ኣንዲልኩ በትህትና ይጠየቃሉ።—

የኢ.ው.ሠ.ኮ.ባ. ጥናትና ምርምር ቡድን
ፓ.ሳ.ቁ 385
አዲስ ኣበባ
ኢትዮጵያ

ጥር 1978 ዓ.ም

CCRDA


ቀለም ብሩሽ
ቧንቧ
የዛፍ ተከላ ስኒ
ፕላስቲክ
ቫዝሊን




CCRDA

ምስል ፬ የጥልቅ ቁፋሮ ውሃ ማውጫ ቧንቧ


CCRDA





ሻፊው የፕላስቲክ ቧንቧ ላይ ከታሰረ በኋላ ወደ ጉድጓድ ውስጥ ይከተኑ

CCRDA

የሚፈለገውን ያህል ቧንቧ ተደራርቦ ወደ ውሀ ጉድጓድ ከገባ በኋላ
በመሬት በሚታየው የቧንቧ መፍቻ ከቋሚ ጋር ማያያዝ









ቧምቧ መፍቻ

ቋሚና ቧንቧው ከተያያዙ በኋላ ማንጠልጠያው ይፈታ!

CCRDA



ፎስፉን ከዘንጉ ጋር የተያያዘበትን ክፍል አጥብቆ ይያዙ!


ቀጥሎ ዘንጉና ፒንቱ በቋሚው ውስጣ ወደ ጉድጓዱ ይወረድ


CCRDA

CCRDA

ጉማ ፣ ሃንጪቱር ሳጭን
ግን ኣስቀድመው
መግባቱ ኣለባቹው!


ቀዋሎ
ከኣጀታው ስብስብ ጋር ኣጥብቆ ይታሠር!





የመጪረሻው ዛጎግ በሚንቢው ፊክ ሉቆርጦ
ጥርስ ይውጣሉት


CRDA



የአርሾ ሰብስብና ቁሚውን የሚያያይዙ
3 ብሎኖች ጠብቀው ይታሠሩ!

CCRDA

ቋሚውን ከአርማታ ጋር የሚያያይዘዉ
አራት ብሎኖች ይታሠራ




CCRDA

የፓምፑን አጀማመር ሳያጣምመው ቁጥር አንድ ወደ ሳይሬ ወደ ታች
ማድረግ ውሀ ያወጣል




ሰላው ውሀ ቦታውን እንዳያቆሽሽ
ከአካባቢው ይራቅ!





የቋሚው 4 ክፍሎች አጠቃቀም

1. በየስድስት ወር ዘይት ይደረግ
2. ክፍሎቹ ብቻ ሳሌ ተው ይገጠማ

CORDA




የፓምፑን የውስጥ አካል መጠገን ካስፈለን

1. ፉ ብሎን ላይ ዘይት አድርግና ቢያንስ ግማሽ ሰአቱ ጠብቅ
2. ካለበለዚያ፡ ብሎን ሊቆረጥ ይችላል!

GEDA



ካሐሉ



ካሐሉ ካተሰበረ ወይም በጣም
ካተበላ ፒሎተኑን በሞላ
መቀየር ይሻላል

ቆዳ

ቆዳው ካተበላ ቆዳውን ብቻ
ቀይር

የቆዳ ማሠርያ


የቆዳ ማሠርያ ካተፈታ
ጥርሱ ላይ ቀለም ቀብያ አጥብቆ
ማሠር ላው

CCRDA



ጊንጊ






የጠፋጣቱ ጠርጉና
የላስቲኩን
አቀማመጥ አስተውል!

ጠፋጣቱ ጠርጉ

ላስቲኩ




ሻልሽ

ሻልሽ የማይሠራ ከሆነ ፈትፉ የተበላሸውን አካል መቀየር ላው

የፓምፑ አካባቢ ሁልጊዜ ንፁህ መሆን አለበት!

ሀዲሩ በፓምፑ እንዳይጫወትበትና እንዳይሰብሩት አዋቂዎች መከላከል አለባቸው!



የሲሚንቶ አርማታ መሰላጣጠቅ ከጀመረ ፓምፑ ስለሚበላሽ ለሚመለከተው ክፍል በፍጥነት ማሳወቅ ያስፈልጋል!

# Afridev /Ibex Installation

The following 10 points detail the main activities that are usually necessary to install an Afridev / Ibex handpump. The steps enumerated in item 1 on well preparation are general and used primarily as a check-list only, while those in 2 through 10 are detailed enough for a normal installation procedure. The eleventh point is also general advice for operation and maintenance of the Afridev / Ibex handpump, or any other pump for that matter.

**1. Well Preparation**

After formal request for water from the village to you , your CPPA's , in co-operation with people from the village, select the following:

a. Water Committee
b. pump care-takers

1.1 Site Selection by water Committee, hydrogeologist, etc.

1.2 Mobilisation

a. Crew and rig , or alternatively, well digging crew , move to site
b. Construction materials on site

1.3 Digging

a. boreholes or auger wells : technicians
b. handdug wells : with help from community

1.4 Water Quality Test

If water quality is too much out of standard and that quality can not be corrected, then stop work and avoid further investment. Site is abandoned in favour of a new one, which again must be selected with the users.

1.5 Well Completion

Install casing
gravel pack
bail and develop
yield test

1.6 Pedestal Construction

apron
pedestal
soak-away pit
fence , cattle-trough, wash basin : made mainly by the users themselves

**Materials**

The building materials usually required are : Cement, sand, gravel, reinforcing bar, water, wood, stones, and moulds for concrete rings and pedestal. The quantity of

SCRDA

consummables is dependent on the particular site and design. Alternative building materials could be selected according to their availability, price and the necessary expertise in the locality.

**2. Pump Selection (in office)**

2.1 Determine whether Shalla (head < 7m) or Ibex, depending on well depth.

If Ibex:

2.2 Set pump handle with proper ratio.

2.3 Choose galvanized or stainless rod, depending on aggressiveness of well water.

2.4 Determine pump setting depth, depending on static water level, well yield , and final pumping water level . A well yield of 0.25 litres per second over, say, a 12 - hour period is sufficient for handpumping. Measure the draw-down at the end of such a yield test, and set your cylinder a couple of meters below this depth. Take special precautions in the wet season because the water level may be too high; it will recede in the dry season leaving your pump dry.

2.5 Determine plastic rope length (to hold riser up during and after installation)

Length = 2 x setting depth + 4m

**3. Riser Installation (on site)**

Meet the selected pump care-takers for the area. All work below is done with their assistance. They get their training for pump maintenance, during installation.

3.1 Ascertain well depth

3.2 Lay out the required length of PVC pipes and steel rods on a clean area. Remember also to place the riser and rod centralizers.

3.3 Prepare for cementing of cylinder with suction pipe.

- remove plunger and footvalve from cylinder.

**3.4 Cementing**

a. Roughen plain and bell ends with sand paper and clean with cotton rag and cleaning fluid. If cleaning fluid is not available, use petrol; but let is dry completely before proceeding to next step.
b. Measure and mark length of bell end on spigot (115mm)
c. Apply a thin coating of solvent cement with brush to roughened bell-end and plain-end.
d. Push plain-end into bell-end fully. Don't rotate pipe during this operation.
e. Wipe excess cement with cotton rag as the excess cement weakens the pipe.
f. Let the joint set for 5 minutes before installation.

CCRDA

### 3.5 Install plastic pipe

a. Cut plastic rope to length required. Burn loose fiber strands to prevent unravelling.

b. Pass half the length of the rope through hole in the suction pipe. Make a knot on each side of hole and pass each length of rope through cylinder centralizer.

3.6 Cement cylinder to first socket of rising main in the usual manner .(see 3.4)

3.7 Lower cylinder and bottom rising main into the borehole.

a. Wrap rope on two diagonal bolts installed on pedestal. (rope carries weight of pipes)

b. Cement remaining riser pipes and lower them down the well.

- don't forget riser centralizer for every pipe
- support the riser from below with pipe clamp or pipe wrench (with two handles) while pushing plain end into bell-end. The plastic rope alone is not strong enough.

